ምዕራፍ ስምንት

ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ የተገጨ ሰው ይዞ የመጣው ታክሲ ነጂ የተገጨውን ሰው በሱብአዊ ርኅራኄ ከመንገድ ላይ አንስቶ ማምጣቱን ካስረዳ በኋላ አድራሻውን ሰጥቶ በደም የተበከለ ልብሱን ውሀ በተነከረ መሀረሙ እየጠራረገ ሲወጣ ላደረገው በጐ ተግባርና ተገቢ የወገንነት ምላሽ ሲስተር ፋናዬ አመሰገነችው ። የምሽት ተረኛ በመሆኗ በድንገተኛ አደጋ ለሚመጡትም ሆነ ተኝተው ለሚታከሙት ተገቢውን ፈጣን እርዳታ ማድረግ ስላለባት ጭንቅላቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን ሰው ጠራርጋ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ካደረገችለት በኋላ ተረኛውን ዶክተር አስጠርታ እንዲያየው አደረገች ። ውስጣዊ ሁኔታውን ለማጣራት የኤክስሬይ ፍተሻ እንደሚያስፈልገው ተነጋግረው ግለሰቡ በሆስፒታሉ እንዲያድር አደረጉ ። ከታክሲ ነጂው ጋር ተጋግዞ ደግፎት የመጣው ጓደኛው ከአልጋው አጠገብ ቆሞ በአዘኔታ የተጐዳውን ሲያይ ትተውት ወጡ ።

በተለያዩ ክፍሎች ያሉትን ሕሙማን ጕብኝታ መርፌና መድኀኒት የሚሰጣቸውን በየሰዓታቸው ሰጥታ ከብዙ ቆይታ በኋላ ወደ ቢሮዋ ስትመለስ ያ ሰው ቀደም ሲል በቆመበት የአልጋ ጠርዝ አጠገብ እንደ ቆመ አካሉን ጭብጥ አድርጐ እንዳቀረቀረ አየችው ። መለስ ብላ መጥታ

የተጐዳውን ሰው ሁኔታ እንደገና ከተመለከተች በኋላ ከባድ የደም መፍሰስ ይታይበት የነበረው ግንባሩ መድማት መቀነሱን አሳይታው ቀስ በቀስ ድማቱ እንደሚቆምና እንደማያሰጋው ነግራው ቢችል ወደ ቤቱ እንዲሄድ መከረችው ። ባለበት ሁኔታ ከጓደኛው አጠገብ እንዲያድር እንድትፈቅድለት በትህትና ጠየቃት ። አልተቃወመችውም ።

የለበሰው ስስ ሸሚዝ ከጉንና ከጐኑ አልፎ አልፎ የተተረተረ ሆኖ ከላይም ሆነ ከታች የደረበበት ልብስ ባለመኖሩ ለብርድ እንዳጋለጠው ይታወቃል ። ሱሪውም ቢሆን ከቁርጭምጭሚቱ በላይ ተጠቅሎአል ። እግሮቹ አልተጫሙም ። ድንገት ላየው ለጭቃ ረገጣ የተዘጋጀ ሰው ይመስላል ። ቀኝ እጁን በስሱ ሸሚዝ ስር አሳልፎ ብብቱ ሥር ከቶት ግራ እጁን ደግሞ ከኪሱ ጨምሮ አንገቱን ወደ ግራ ትከሻው ዘንበል አድርጐ በአዘኔታ እይታ በደም የተበከለ ነጭ ሻሽ የጠመጠመውን ጓደኛውን ሳይሰለች ይመለከተዋል ።

ይህንን ሁሉ ሁኔታውን ከሌላው አሻጋሪ ቢሮዋ ሆና ስትመለከተው የነበረችው ሲስተር ፋናዬ የሚሞላ ቅጽ መኖሩን ነግራው ወደ ቢሮዋ አስከትላው ተመለሰች። ያለችውን ቅጽ አውጥታ በቅድሚያ አደጋ የደረሰበትን ሰው ማንነትና ቀጥሎም የጓደኛውን ስምና አድራሻ ጠይቃ ነግሯት ጻፈችው ። በዚህ ጥያቄና መልስ ውስጥ ነበር ልታስታውሰው የቻለችው ። ገጽታውንና ቁመናውን አይታ ባለማስታወሳ ገረማት ። ችግር በጠንቁ ከፉኛ አጕሳቁሎታል ። ማወቋንና ማስታወስዋን ሸሸጋ ፤ ጥያቄዎቿን ስትደረድር ቆይታ የምትጽፈውን ጽፋ ስታበቃ አቶ ሀብቴ ዳዲ ከመውጣቱ በፊት በስፌቱ የታጠፈውን ጋቢዋን ከወንበሩ ላይ አንስታ ከትከሻው ላይ አለበሰችው ። የልብ

ሱን መቆሸሽ እያጋነነ ጋቢውን ሊያገሎድፈው እንደሚችል እያጥላላ የደረበችለትን ገፎ ሊያስቀምጥ ክምሩ ታገላት ። በተግሣጽም በማግባባትም አሸንፋው ጋቢዋን ከትከሻው ደርቦ የሚቀመጥበት አንድ ወንበር ይዞ ጓደኛው ወደ ተኛበት ክፍል ሄደ ። ሲስተር ግን ክፉኛ በሀሳብ ተመስጣ ሲጋራዋን እያጨሰች አቶ ሀብቴ ዳዲንና ሀሊናዋ የሚያውቀውን እውነት እየተመለከተች በተቀመጠችበት ብዙ ቆየች ። ውብሸት እንዳይላሉ መርፌ የሚወጋበት እኩለ ሌሊት መድረሱን አስታውሶ በዚያውም ብቅ ሳትል መቆየትዋ አሳስቦት መኩሪያ ወደ ቢሮዋ ፍለጋ መጣ ።

መኩሪያ ወልደሩፌ ያገኛት በሚያሳዝን ሁኔታ በትካዜ ተሰብራ ነበር ። የሱ ድምጽ ከተዘፈቀችበት የሀሳብ ባህር ጉትቶ አወጣት ። ልባዊ በሆነ አዘኔታ ምን እንዳጋጠማት ተጨንቆ ጠየቃት ። በዚህ መሰሉ የመንፈስ ስብራት አንክሳ ፤ በሀዘንና በትካዜ ገጽታዋ ጠቁሮ አይቷት አያውቅም ። ሲስተር ፋናዬ ለምንም ነገር የማትደነቅ የማትጨነቅ ሕይወትን ቀላል በሆነ የአኗኗር ዘይቤ የምትመራ አቋሟንና ፍላጐትዋን ለመግለጽ ነጻ ስሜቷን የምትመረኮዝ ይህም ሁኔታዋ በኅብረተሰቡ ውስጥ እምብዛም ያልተለመደና ያልተወደደ በመሆኑ አጉል ግምት የሰጣት እንደሆነች ብዙ ተከታትሎና ታዝቦ የተረዳው ነው ። በዚያ ምሽት ግን በማንኛዋም ሴት ላይ የሚታየው የሆደ ባሻነት ባህሪ ተጠናውቷት አየ ። በውስጧ አምቃ ትቆጣጠረው የነበረውን እርግጠኛ እሷነቷን የሚሸፍነው ጠንካራ ስሜቷ ላልቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ዐይኖቿ በእንባ ረጥበው ተመለከተ ። አሳዘነችው ።

እቅፍ አድርጐ አካሏን በእጆቹ መንፈሷን ፤ በቃሉ በመዳሰስ ሊያጽናናት አሰኘው ። ሥፍራውና ጊዜው አል

ፈቀዱለትም ነበርና በቢሮዋ ውስጥ የሚገባትን ክብርና አቀራረብ ሳያጓድል ቆሞ ተጠቦ ተጨንቆ ምን እንደሆነች ደጋግሞ ጠየቃት ። የተሰማትን የሆነችውን ለመናገር ፈቃደኛ ስላልነበረች ጥያቄውን አድበስብሳ ፤የሙያ መሣሪያዎቿን ይዛ ለውብሸት እንዳይላሉ የታዘዘውን መርፌ ለመውጋት ከቢሮዋ ወጣች ። መኩሪያም ተከትሏት ተመለሰ ። ውብሸት እንዳይላሉን በለሰለሱ ቃላት እያበረታታች ፤ መርፌውን ከወጋችው በኋላ መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው አስታማሚዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ አካሉን ደባብሳ በወጉ አልብሳና ፈገግታዋን አሳይታው ሌላ መርፌ ለመውጋት ወደ ሌላ ክፍል እንደምትሄድ አሳውቃ በሩን ዘግታ ወጣች ። ፈገግታዋ ግን ቅሬታ የሰረጸው ስለ ነበር በገጿ ላይ አልፈካም ። ውብሸት እንዳይላሉም ልብ ብሎ ታዝቧት ነበር ።

ሲስተር ፋናዬ የሄደችው ወደ ሌላ በሽተኛ ክፍል ሳይሆን በቀጥታ ወደ ክፍልዋ ነበር ። የሙያ መሣሪያዎቿን ከጠረጴዛው ላይ አኑራ ወንበሯ ላይ ጭብጥ ብላ ከተቀመጠች በኋላ ሲጋራዋን አቀጣጥላ ሁለት ጊዜ ጠንከር አድርጋ ሳበችው ። በጣቶችዋ መካከል የሰካችውን ሲጋራ ከጸጉርዋ አርቃ እንደያዘች በሁለት እጆችዋ መዳፍ ጭንቅላትዋን ደግፋ አቀርቅራ ዐይኖቿን ጨፍና ወደነበረችበት ሀሳብ በመመለስ ላይ ነበረች ።

"ፋኑ ለምን ታርቂኛለሽ" አላት መኩሪያ ከፊት ለፊቷ ቆሞ ሁኔታዋን አቀርቅሮ እየተመለከተ ። ዐይኖቿን ከመግለጧ በቀር ካቀረቀረችበት ቀና አላለችም። "ከማንም የበለጠ ወደ ሕይወቴ ያቀረብኩት አንተን ነው ። አንተም ብትሆን ቀረቤታህ በተወሰነ ርቀት ላይ ይታገዳል"

"የስሜትሽና የሀሳብሽ ተካፋይ እንድሆን ክብሩንና ዕድሉን ለምን አትሰጪኝም"

“ ያ ዕድል አስቀድሞ ተሰጥቷል ”

“ ለማን”

“ ለሲጋራዬ ” የተከማቸውን የሲጋራዋን አመድ መተርኮሻው ላይ አራግፋ በጥማት ስሜት ደጋግማ ማገችው ። ወደ ውስጧም በተነችው ። ያለ አንዳች ተጨማሪ ቃል መኩሪያ ወልደሩፌ ወደ ውብሸት እንዳይላሉ ክፍል ተመልሶ ሄደ ። ውብሸት በእንቅልፍ አሸልቦ ስለነበር በስተግርጌ ካለው ወንበር ላይ እግሮቹን አነባብሮ ተቀምጦ መኩሪያ በጸጥታ ሀሳብ ማባዘት ጀመረ ።

ሲስተርም አስባ አሰላስላም ለግላዊ ውሣኔዋ የፈለገችውን ብቸኝነት ለተከታታይ ሰዓታት በጥሪና በሰዎች መምጣት ሳትረበሽ ስላገኘች ሀሳብዋንና ትካዜዋን ማሰሪያ አድርጋለት ተነሣች ። በመኪና ግጭት የተጐዳውን ሰው ለሶስተኛ ጊዜ ልታይ ሄዳ እንደገና በጥንቃቄ በልብምት ማዳመጫያዋና በሙቀት መለኪያዋ መረመረችው። ወደ ውጭ የሚፈሰው ደም የታገደ ቢሆንም ውስጣዊ ድማት እንደሌለው ለማረጋገጥ ነግቶ የኤክስሬይ ፍተሻ እስኪደረግለት መንፈሷ ቸኮለ ። አዘማሚያው አላማራትም ። ከአልጋው አጠገብ ተቀምጦ አይን አይኑን የሚያየውን ሀብቴ ዳዲን ልብ ብላ እያስተዋለች በአንደበትዋ ግን እያጽናናችው ቆይታ ወደ ቢሮዋ ተመለሰች ።

ቀሪውን ሌሊት ቀን ቀን እየተኛ ሌሊት በንቃት ከወዲያ ወዲህ ከሚለው ፤ በአጉል አፈጣጠር ዐይኖቹ ከጉድጓዳቸው ወጥተው ተንጠልጥለው ካበጡበት የአስራ አራት ዓመቱ ልጅ ጋር ስታወራ አሳለፈችው ። ቀን መተኛቱን ሌሊት መንቃቱን ለምን እንደ ለመደውና እንደ ወደደው ሲጠየቅ ፤ ተፈጥሮ የበደለችው ስንኩል ኅብረተሰቡ በሚያሳየው የመሸሽና የፍራቻ ሁኔታ ከሚጥሉበት

ቅስም ሰባሪ አባባሎች ራሱን ለማገለል ያደረገው መሆኑን ይናገራል ። በሕጻንነቱ ከፈፋ ውስጥ ተጥሎ ተገኝቶ ለሆስፒታሉ የተሰጠ በመሆኑ ኑሮውና ሕይወቱ ከሆስፒታሉ የተጣመረ ነው ። ከብዙዎቹ መካከል ሲስተር ፋናዬን ለይቶ ይቀርባታል ። ከማንም የበለጠ አጥንቶ ስለሚያውቅ የውሎና የአዳሯን ፕሮግራም ተከትሎ ከሷ ጋር መቆየቱን መጫወቱን ይደሰትበታል ። ተፈጥሮ በለገሰችው ባለው ሁኔታው በዓለም ላይ ተደስቶና ራሱን ዝቅ ሳያደርግ መኖር እንዳለበት ሌሎች መሰል ምሳሌዎችን እየጠቀሰች የህሊና ብርታት ስለምትሰጠው መጽናኛው አድርጎ ተቀብሏታል ።

በበነጋው የሰንበት ማለዳ ላይ ተረኞች የሕክምና ሰራተኞች ሲገቡ የምትተካትን አስታማሚ በአደራ ተማጽና በመኪና የተገጨውን ሰው ሁኔታ አስረድታት በጥንቃቄ እንድትከታተልላት አሳስባ ወጣች ። የሄደችው ወደ ውብሸት እንዳይላሉ ክፍል ነበር ። በእንቅልፍ እጦት ዐይኖቹ ቀልተው ፊቱን ከብዶት የነበረው መኩሪያ ብቻ ሲሆን ውብሸትና ሲነጋ የመጣው ወንድሙ ሣህለ ድንግል ንቃት ይታይባቸዋል ። መታጠቢያ ክፍል አድርሰውት ተጸዳድቶ መመለሱ ስለነበር ውብሸት አልጋው ላይ ተቀምጦ በቀኝ እጁ የደነዘዘውን ግራ እጁን እየደባበሰ አየችው ። የንጋት ሰላምታ ሰጥታቸው ከተቀላቀለች በኋላ ስለሚሰማው ውስጣዊ ስሜት ጠያይቃው ለሚሰጣት መልስ የጭን ቅላቱን እንቅስቃሴ እየተከተለች ውብሸትን ካነጋገረችና ከተረዳች በኋላ ወደቤትዋ ለመሄድ መሰናዳትዋን በመግለጽ መልካም ቀን ተመኝታላቸው ወጣች ። ጥቂት ቆይቶ መኩሪያም ተከተላት ።

በእንቅልፍ እጦት አሁንም አሁንም እያዛጋ መኪናውን ከሆስፒታሉ ግቢ እያሽከረከረ ወጣ ። መሄድ ስላሰ

CamScanner

ኛት ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እንዲያደርሳት
ጠየቀችው ። በዱሮው ቁራ በኩል አድርጐ ዳገቱን ከወጣ
በኋላ ከሥላሴ ቤተክርስቲያን ደረሱና ከምእመናኑ ተቀ
ላቀሉ ። ወደ ቤተ መቅደሱ ገብታ ቆይታ ለማድረግ እን
ደፈለገች ገልጻለት ወደ ቤቱ ሄዶ እረፍት እንዲያደርግ
አሳስባው ተለያዩ ። ጫማዋን አውልቃ ከደጃፍ ሰላሙ ጥግ
አኑራ ፤ወደ ውስጥ እስክትገባ ድረስ በዐይኖቹ ተከተላት።
ወዲያው ያወለቀችውን ቀይ ጫማ ልትሳለም ያጐነበሰች
ሴት ሸፍናው ቀና ስትል ከሥፍራው አጣው ። መኩሪያም
ከመኪናው ተንደርድሮ ወርዶ የሴቲቷን አቅጣጫ ተከትሎ
ፈጥኖ ተራመደ ። አንጠልጥላው የነበረውን ከረጢት
ከእግሯ ሥር አኑራ የጽድ ዛፍ ተደግፋ ነጠላዋን ከአፍን
ጫዋ ላይ ጥላ ሽቅብ ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅርጻ ቅርጽ ዓይ
ኖችዋን ስታቁለጨልጭ ደረሰ ። " ወገኔ ስለ ሰንበት
ምጽዋት ጣሉልኝ ፤ ቁራሽ ጣሉልኝ" የሚል ደሀ ከረ
ጢቷ ላይ ዓይኑን ተክሎ ይለምናታል ። ያለ አንዳች ጥያ
ቄና ትእግስት ከእግሯ ሥር ያለውን ከረጢት አንስቶ የከ
ተተችውን ጫማ መዞ አወጣው ። ከረጢትዋን እንኳን
ለመቀበል አልሞከረችም ። ትታው ወደ ወወክማ በሚያ
ወጣው በር ሮጣ ተሰወረች ። ቁራሽ ሲለምን የነበረው
ደሀ መኩሪያ የወረወረውን ከረጢት አንስቶ አገላብጦ
እያየ ለሌላ ልመናው ዛፍ ተጠግተው ወደሚጸልዩት
ሌሎች ሰዎች እያነከሰ ተሻገረ ።

መኩሪያም መኪናውን በስተምዕራብ ጠርዝ ላይ
ጥግ አስይዞ ቆሞ የሲስተርን መውጣት ይጠባበቅ ጀመር።
የመንፈስ ድርቀት ሲሰማትና ሆድ ሲብሳት ህሊናዋን
ለመጠገንና ለማለዘብ የምትመርጠው ቤተ እግዚአብሔ
ርን በመሆኑ ፤ በዝማሬው ቃና በጸሎት ቃላቱ ፤ በምልጃ
ሥርዓቱ ፤ በአማኒው ሁኔታ ውስጥ መደባለቁ ይፈውሳ

ታል ። ማንኛውም ነገር ቀሪና አላፊ መሆኑን ይበልጥ
ትገነዘብበታለች ። በዚህም ኑሮዋንና ሕይወቷን ከጭንቀት
ነጻ አድርጋ ለመራመድ ትነቃቃበታለች ።

ቅዳሴው ተካሂዶ ሥርዓተ ቁርባኑ ተፈጽሞ አሜን
ተብሎ ቄሱ ከባረኩ በኋላ በቅኔ ማኅሌት ዝማሬና ዕጣነ
ሞገር ተሰምቶ ሲያበቃ ዲያቆኑ ' እትው በሰላም' ን እንዳ
ሰማ ሕጻናቱና አረጋውያኑ ቆራቢዎች አፋቸውን በጨ
ርቃቸው ይዘው ሲወጡ የገባው ሁሉ ለመውጣት ተጣድፎ
ሲጋፋ በተቀመጠችበት ረግታ ስትመለከት ቆየች ። የቅ
ዳሴ ጸበል የያዘ ዲያቆን በአጠገቧ ሲያልፍ በእጅዋ ላይ አን
ቆረቆረላት ። በመዳፍዋ ያቋተችውን ጸበል ጠጥታና ተባ
ብሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጭር ያለውን ቤተ ጸሎት ዙሪያ
ውን እየማተረች በዝግታ ወደ ውጭ ወጣች ። ጫማዋን
ካስቀመጠችበት ስታጣው በዓይኖቿ አካባቢውን አጥብቃ
ቃኘችው ። መጥፋቱን አረጋግጣ ያጠለቀችውን የእግር
ሹራብ አውልቃ የመገረም ፈገግታ አጥልቃ ታቹን ወደ
ባለ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ወደ ሚያወጣው በር
አቅጣጫ በባዶ እግሯ ዝግ ብላ መንገድ ጀመረች ። ከት
ልቁ ማርገጃ ወርካ አጠገብ ስትደርስ ከኋላዋ የመኪና
ጥሩምባ ሰምታ መንገድ ለቃ እልፍ አለች ። መኪናው
በዝግታ አጠገቧ ሲደርስ በሩን ከፈተላት ። ቀና ብላ አይ
ታው ገባች ። የጫማዋን መጥፋት በመገረም ነገረችው።
የአጠፋፉንና የአመላለሱን ሁኔታ እሱም እየተገረመ አወ
ራላትና ቀዩን ጫማዋን አቀበላት ። የእግሯን አቧራ አራ
ግፋ ተጫማችው ። ከግቢያቸው በር ላይ ካደረሳት በኋላ
ማምሻውን እንደሚመጣ አስታውቋት ወደ ቤቱ አመራ ።

ምንጊ የሲስተርን መምጣት ስትጠባበቅ አለወ
ትሮዋ በማርፈድዋ ሰግታ ስትንቆራጠጥ ነበርና በሩን
ስታንኳኳ በደስታና በእፎይታ ፈጥና ከፈተችላት ። እዚ

CamScanner

ያው እበሩ ላይ ከሩቅ አገር እንደመጣች ሁሉ ከወዲያ ወዲህ አገላብጣ ሳመቻትና የያዘችውን ቦርሳና ያንጠለጠለችውን ላስቲክ ተቀብላ አስገባቻት ። ስልጡንና ቀና ልጅ ውላ ለመጣች እናቷ የምታደርገውን ዓይነት መስናዶ አድርጋ በፈጠነ አቀራረባ ቁርስ አብልታት የሰንበት ማለዳ ረጋ ያለ ቡና ለማፍላት ተዘጋጀች ። ሲስተር ሥራ ላይ አድራ ስትመጣ ቡናውን የምታሸተው አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ ጋቢዋን ተጐናጥፋ ከፍ ያለ ትራስ ተን ተርሳ ፊት ለፊት ከነረከቦቱ ምንቴን እያየቻት በመሆኑ በዚሁ ሁኔታ ከጠባብዋ የመጋረጃ በስተጀርባ ቦታ ላይ ቡናና እጣኑ ተጨጫሰ ። ከበነጋታው ሰኞ ጀምሮ ሥራ እንድትቀጥል የተሰጣትን ደብዳቤ በደስታ እንደፈካች ከኮመዲኖው ላይ አንስታ አቀበለቻት ። ሲስተርም የደብዳቤውን ይዘት ካየች በኋላ ከተኛችበት ዘላ ተነስታ አቅፋ ሳመቻት ። ጐረቤታቸው አሥራት ማንደፍሮ ባለውለታቸው መሆኑን አጠንክረው ቢያወሱትም ስለሚመልሱት ወሮታ ግን መናገር አልቻሉም ።

ከአቦሉ ቡና ቀድታ ከተቋደሱ በኋላ ሲስተርን እንቅልፍ ጥሏት ስትተኛ ምንቴ ለመንደር ንዑስ ኮሚቴ ስብሰባ ወጣች ። የንዑስ ኮሚቴውን መዋቀር የወሰነው የዋናው ዕድር ስብሰባ ነበር ።

ስልኩ ዶጋግሞ ቢያንቃጭልም ሲስተር ከባድ እንቅልፍ ጥሏት ስለነበረ አልነቃችም ። ሲስተር ፋናዬን የተካችው አስታማሚ በአደራዋ መሠረት ስለ ሕመምተኛው ሁኔታ ልትገልጽላት የደወለችው ነበር ። ምንተስኖት በንዑስ ኮሚቴ ምስረታ ላይ በተደረገው ምርጫ በተመራጭነት ገብታ መሥራት እንዳለባት ብዙዎቹ ሴቶች የሴቶች እድር ሰብሳቢነቱን ለሷ ጸሐፊነቱን ለአበባየሁ አደላድለው ኮሚቴው እንዲመሠረት አደረጉ ። በኮሚቴው ውስጥ የተሰጣ

ትን የሥራ ድርሻ ምክንያት ተመርኩዛ አጥብቃ ብትቃወምም የመንደሯ ሴቶች የመልካም ጉርብትናና የማቅረብ ተጽዕኖ ስላደረጉባት ከራስዋ ሊወርድ አልቻለም ።ጠልቶ መሸከም ሆነባት ። አጋጣሚዎች የሚፈጥሩትን የረቀቀ ስልት እያሰላሰለች የእሷና የአበባየሁ በአንድ ኮሚቴ ውስጥ ለአንድ ዓላማ ተሰልፎ መስራት እስከ መቼና እስከምን ደረጃ እንደሚሆን እያሰበች ሳቀች ።

የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታቸው የሳሳው የግቢው ሴቶች ወግ ባለው ሁኔታ መሰባሰቡን ወደውትና አምነውበት የሚያስተዳድራቸውን ሕግና ደንብ ነድፈው በውዴታ ግዴታ ራሳቸውን ሊያስገዙ ፈቅደው አመራር ሰጪዎችን መርጠው የጥሩ ጅምር መሠረት ጥለው ወደ የቤታቸው ሲመለሱ ምንቴም በዚህኛው አጋጣሚ እየተደነቀች ከቤቷ ደረሰች ።

ምን ተስኖት ስትገባ ሲስተር እንቅልፏን ከፍላ ነቅታ ነበርና ገና እንደገባች ስለ ቆይታዋ ጠየቀቻት ። እንዲያውበደፈናው ፡ “ ወይ አለመተዋወቅ አሉ ሌቦ ሣህሉ ” እያለች ሲስተር ወደ ተኛችበት ክፍል ገብታ ከአልጋው ላይ ቁጭ አለች ። ሲስተርም ሳቅዋ ተጋብቶባት አብራት ፈገግ እያለች ፤

“ማናቸው ሌቦ ሣህሉ” አለቻት ሲስተር፡ምንቴም ስለ ሌቦ ሣህሉ የሰማችውን አፈታሪክ መልሳ ልትተርክላትና የነገሯን ጭብጥ ልታስረዳት ተዘጋጀች ።ግርም እያላት ፡ “ ሌቦ ሣህሉማ በጐንደር አካባቢ እንደኖሩ የሚነገርላቸው የታወቁ ሌባ ነበሩ ። በአንድ የገበያ ቀን ስማቸውንና ዝናቸውን እንጂ መልካቸውን የማያውቅ ገበሬ ጠጋ ብሎ ሌቦ ሣህሉ ገበያ ውስጥ መታየታቸውን እያስጠነቀቀ፤ የአቅማዳ እህሉን በአደራ እንዲጠብቁለት ሰጥቷቸው ወደ

CamScanner

ሚደርስበት ድርሶ ሊመለስ ይሄዳል ። አደራውን የተቀበሉት ሌቦ ሣህሉ እህሉን ሲጠብቁለት ቆይተው ለየዋሁ ባላገር ሲያስረክቡት “ ወይ አለመተዋወቅ” ሌቦ ሣህሉ ማለት እኔ ነኝ “ብለውት ሄዱ ። እየተባለ ብሂላቸው ከሰው ሰው እየተሸጋገረ ይነገርላቸዋል ። ” ብላት ከት ብላ ሳቀች ሲስተርም በቃሉ አገላለጽና በታሪኩ አመሠራረት ተገርማ አብራት እየሳቀች ከዚህ ጋር የተያያዘ ወይም የተመሳሰለ ምን ጉዳይ እንዳጋጠማት ምንቴን ጠየቀቻት ። ምንቴም በሴቶች እድር ውስጥ እሷ ሰብሳቢ የውብሸት እንዳይላሉ ሚስት ጸሐፊ ሆነው መመደባቸውን ስትነግራት “ወይአለ መተዋወቅ ”እያለች ሲስተርም ከልቧ ፍንቅል ብሎ በሚወጣ ሳቅዋ ቤቱን ሞላችው ። ከምሳነቱ ይልቅ በመክስስነቱ የሚታሰብ በዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ እህል ቀማምሰው ምንቴም ስላገኘችው ሥራ አጀማመር ፤ ሲስተርም ማታ ስላጋጠማት ሁኔታ ሊያወሩ ተደላድለው እንደተቀመጡ ፤ የስልኩ ድምጽ አንቃጨለ ። ምሽቱ ላይ ስላጋጠማት የተጎዳ ሰው እንድትደውልላት አደራ ያለቻት ነርስ የደወለች መስሏት ሲስተር ፈጥና አነሳችው ። በቁጥር ስህተት የተደረገ ጥሪ ነበርና መልሳ ዘጋችው ። የመኪና ድምጽ ሰሙና ጆሮአቸውን አቅንተው መጪ ወይም አላፊ መሆኑን ለማወቅ ጠበቁ ። የኮቴ ድምጽ ሲሰሙና በራቸው ሲንኳኳ መኩሪያ መሆኑን አልተጠራጠሩም ። በሩን ሲስተር ፋናዬ ከፍታ ብቅ ስትል አቧራ ከለበሰ ፊቱ፤ ከተንጨበረረ ጸጉሩ ጋር ከመስክ ሥራ የተመለሰውን ጐረቤትዋን አሥራት ማንደፍሮን አገኘችው ።

ያላሰበችው ሰው ስለነበር ደንግጣ እንዲገባ ጋበዘችው ። ግብዣዋን ሳይቀበል በግራና በቀኝ እጁ ያንጠለጠለውን ዕቃ አቀብሏት ተቻኩሎ ወደ ቤቱ ሄደ ። የሚለ

ውጠውን ልብስ በትንሽ ቦርሳ ውስጥ አድርጐ በመኪናው እንደገና ወጣ ። የአሥራት ጉዞ ወደ ፍልውሀ ነበር ።

ሲስተር የተቀበለችውን ጥቅል ዕቃ ከምንተስኖት ጋር ገላልጠው ካዩ በኋላ የበዓሉን መድረስ አስታወሱት ። ከሁለት ሣምንት በኋላ የፋሲካ በዓል ይከበራል ። አስራ አንድ ሰዓት ላይ መኩሪያ ሲመጣ ምንቴ ሆን ብላ ወደ አፍንጮ በር እናትዋን ጥየቃ ወጣች ።

በልዩ ልዩ አርእስት ላይ ሲነጋገሩ ቆይተው መኩሪያ ቀስ በቀስ አስቦበት ወደ መጣበት ጉዳይ ንግግሩን አስተካከለ ። ለመነሻ የማታውን ሁኔታዋን አስታውሶ ምን ችግር ገጥማት እንደነበረ ገልጾ እንድትነግረው ሲስተርን ለመናት ። አሸሽታ ያስቀመጠችውን የሕይወቷን ክፍል የሚነካና ልትናገረው የማትፈልገውን ገመናዋን የሚጠቁም በመሆኑ ይህን ጥያቄውን ላለመቀበል ወስና ድካምና ፤ ግጭት የደረሰበት ሰው አዘኔታ ተደራርበው መንፈሷን እንደ ለወጡት አመካኝታ በጥቅሉ ተወችው። አልመስልህ ስላለው አልተቀበላትም ። በእልፍ አእላፍ ሰዎች መካከል እየተመላለሰች ከሰው ጋር እየኖረች ነገር ግን በብቸኝነት ምድረ በዳ ብቻዋን እንደምትንገላታ ፤ ነፍሷ በባይታወርነት እንደምትባዝን ፤ መረዳቱን ገልጾላት የምታደርገው የመንፈስ ሽሽት አግባብ አለመሆኑን አስረድቷት እንደ ገና የሕሊናዋን እውነት በጓደኝነቱ አምና እንድታካፍለው ጠየቃት ።

በተወሰነ ርቀትም ቢሆን መኩሪያን ከማንም በተሻለ ሁኔታ ማቅረቧ ከውስጧ ባስነደዳት ልዩ ኃይል ሲሆን ያ ኃይል አሁንም ግፊትና ተጽዕኖ እየደረገባት የጠበቀው የህሊናዋ ውሳኔ ሲላላ ተሰምቷታል ። ሆኖም ልትታገለው ወስና ለዝግ ምላሸዋ ታጠቀች ። ይህንን ውስጣዊ

ስሜቷን እየፈተሸች ስታሰላስል መልስ ሳትሰጠው ስለ ቆየች እንደገና ፤

" ባለን መቀራረብ በንጹህ መንፈስ ግንኙነታችንን ማጠንከር አንችልም " አላት ከረር ባለ ጥያቄ ፤

" ከያዝነው ደረጃ ሳንሻገር ይቻላል "

" ከዚህ ደረጃ ከፍ ቢልስ "

" የማልቀበለው የማልከተለው ይሆናል "

" ለምን"

" ራሴን ለዚያ ሁኔታ አላዘጋጀሁም ፤ ለዚያም አል ታደልኩም "

" ችግሩን ልወቀዋ "

" ችግሬን ለመወጣት በግሌ ከምጥር በቀር ለማንም ላሳውቅ ፈቃደኛ አይደለሁም አውቃለሁ ምናልባትም ብትሰማው ልትሸሽኝ እንደምትፈጥን "

" ነፍሴን ለምን በጉጉት ታንጠለጥያታለሽ ውሳኔው ን ለኔ ተይውና ከባድ ብለሽ የያዝሽውን ችግር ልስማው"

" ጉጉት የሰዎች የተፈጥሮ ባህሪ ነው ። ያጓጓህ እኔ ነቴ ብትሰማው ሊያርቅህ ካልሆነ በቀር የሚጥም ወይም የሚያረካ ታሪክ የለውም "

በዝምታ ተውጠው ሁለቱም አቀርቅረው ቆዩ ። ከኪሷ ውስጥ ክብሪት አውጥታ በከንፈሮችዋ መካከል ለያዘችው ሲጋራ ማቀጣጠያ ልትጭር ስትዘጋጅ እጆች ዋን አጣምሮ ይዞ ዐይን ዐይኗን እያያት ፤

" ከማንኛውም ችግርሽና ጉዳትሽ ጋር ለቀሪው ሕይ ወቴ እመቤቴ ሁኚ ፤ ባለኝ አቅምና ሙሉ ፈቃድ የማይ ቆጠብ ጓደኝነቴን ተቀበይኝ " አላት ። ፈገግታው የፈጠ ራቸውን የጉንጮቹን ስርጉዳት ልብ ብላ አስተውላ ዝም

አለችው ። " መልስ ስጭኝ" አላትና በእርጋታ ወዘወዛት በከንፈሯ ላይ የያዘችውን ሲጋራ አሳየችው ለመናገር እን ዳልቻለች ተገንዝቦ በአፉ ተቀብሏት ወደ ጐን ሰፋው ላይ ጣለው ።

" ጓደኝነትህን እወደዋለሁ ። አሁን ባለበት ደረጃ ን ስከሆነ ድረስ አንለያይም ። " አለችው ቅጭም ብላ ።

እጆችዋን ለቀቀና የራሱን ንጹህ ሀሳብ ገልጾላት ለመውጣት ስላሰበ ፊቱን ኮስተር አድርጐ ከተቀመጠበት ተነስቶ ውጪውን እያየ እጆቹን ከግራና ቀኝ የሱሪው ኪሶች ከትቶ ቀጠለ ።

" የገለጽኩልሽን ሀሳብ ያቀረብኩት ቀሪውን ሕይ ወቴን አንቺ የተሟላ ታደርጊዋለሽ የሚል ጠንካራ እም ነት በልቤ ውስጥ ስላንሰራራና ስለ ወተወተኝ እንጂ ፤ ትዳርና አባወራነቱ የታሰበልኝ ማድረግም የነበረብኝ ቀደም ሲል ነበር ። በተለይም የኔን ትዳር መመስረት የምትመኘው እናቴ ረዥም ዘመን ለምናኛለች ። አስለም ናኛለች ። ቢሆንም ያልተቋረጠ ጥሪዋ መንፈሴን አላነ ቃውም ። የአንቺ ተፈጥሮና ሁኔታ ስቦኝ ከቀረብኩሽ ወዲህ ግን ፍላጐት በውስጤ ተጠነሰሰ ። ሀሳቤን በጥሞና መርምረሽ ብትቀበይኝ ደስታዬ ነው ። ትንደእኔም የሚያ ውቁን ሁሉ ይደሰታሉ ። በተለይ እናቴ ትረካለች ። "

" ሌላው ቀርቶ ይህ አባባልህ እንኳ ያመኛል "

" የትኛው " አላት መለስ ሳይል ፤

" እናቴ፣ ስለ እናቴ፣ ለእናቴ እያልክ የምታወራው" ገርሞት ፈጥኖ ወደ እሷ ተመልሶ ፤

" ስለ እናቴ መናገሬ ያስከፋሻል "

" አዎ"

" ለምን"

" እናት የሚለው ቃልና በዚህ ቃል ሳቢያ የሚኖረውን ግንኙነት ጭራሽ መስማት ስለሚያስጠላኝ "

" ለምን "

" ቃሉ የሚደነቁለው ቁስል አለኝ "

" ምን ማለትሽ ነው ከእናት የበለጠ የሚወደድ ምን ይኖራል "

" እኔ ግን ' እናት ' የሚለውን ቃልና ቃሉም የሚፈጠርበትን ግንኙነት አያይዤ የምጠላ ነኝ ፤ በዚህ ልዩነቴ ኅብረተሰቡ ቀርቶ ዓለም ቢያሸሽኝ አይደንቀኝም እስቲ እናት ለምትለው ቃልና ግንኙነት ያመንክበትን መግለጫ ስጠኝ " አለችው ። እጅግ ገርሞት ተመልሶ ቁጭ ብሎ አስተዋላትና የሚሰማውን መናገር ጀመረ ።

" የኔ አገላለጽ በግላዊ ስሜትና ከእናቴ ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ ተመርኩዞ ይነሳል ። እናት ማለት ፤ የሕይወት መሠረትና የእውነተኛ ፍቅር ገጽታ የሚታይባት ወሳኝ አካል ናት እላለሁ ።" አላት

"ይህ ገለጻህ ተጨባጭ የሆነበትን ድርጊት አሳየኝ ፤ አስረዳኝ "

" ጥሩ ፣ እናት ሕይወት በሕይወቷ ውስጥ ካንሠራራበት ቅጽበት ጀምሮ እስከ ፍጻሜዋ ድረስ ለወለደችው ልጅዋ ለአካል ፤ ለአእምሮ ፤ ለኑሮ እድገቱ ባልተቆጠበ ጥረት መሠረቱን ታንጻለች ። በዚህም ተግባሯ እውነተኛው የፍቅር ባህሪና ገጽታ ይከሰትባታል ። ከሷ ይልቅ ለልጅዋ ጉልበትዋን ጊዜዋን ሙሉ ፈቃድዋን ይዞታዋን ጭምር ትሰዋለች ። በመስጠቷ ትረካለች ። ይህች ቸር ፍጡር ያልተወደደች ማን ይወደዳል ታዲያ "

" የገለጽከውን ቸርነትና እንክብካቤ የዳሰስከው የጨበጥከው ከሆነ ልትሟገትለት ይገባል ፣ የዘረዘረከውን

ድርጊት ማየት ቀርቶ በቃላት ስልት እንኳ ያልሰማ ያላለመ ተወላጅ ያንተን ስሜት እያስተጋባ በተጋቦት ወግ ሊመጸደቅ አይችልም ። ስሜቱንና ጭብጡን ተመርኩዞ የራሱን ትርጉምና ስያሜ ይሰጣል እኔ ንናቴን ' የቅጣት ጨንገር' ብላት የሚስማማኝ ሆኖ አገኘዋለሁ ። ስለዚህም ባለኝ ጥላቻ መምረር የተነሳ ቃሉን መስማት አልወድምና ባታነሳብኝ "

" እናትሽ ያደረሱብሽ በደል እንዳለ ብትገልጭልኝ አባባልሽ ስሜትሽን ያስረዳኝ ይሆናል አለበለዚያ ግን ለእናቶችና በተለይም ለእናቴ ያለኝ ትርጉም ከገለጽኩልሽ ሁኔታ ጥቂትም ፈቀቅ አያደርግኝም ። "

ጥላቻ በሰረገበት ትዕግሥተ መኩሪያ የተናገራቸውን ቃሪት እያስጠሏት ሰማቻቸው ። ከዚህ በኋላ ነገሩን አራዝሞ መነጋገሩን ስላልፈለገች ቆም ብላ አየችው። ለጥያቄው መልስ የሚሻ ስለነበር እሱም ዓይን ዓይኗን እያየ ጠበቃት ። ከተቀመጠችበት ተነስታ ሲጋራዋን እያጨሰች በመስኮቱ አሻግራ በእንግሊዝ ኤምባሲ በስተጀርባ ያለውን አነስተኛ ተራራ አሻግራ እየተመለከተች ቆይታ በሀሳብ ተሰወረች ። ዝም ብሎ ለረጅም ጊዜ ተመለከታትና ልቡ በአዘኔታ ተሞላ ከተቀመጠበት ተነስቶ አገጩን ከትከሻዋ ላይ አሳርፎ ትከሻዋን በሁለት እጆቹ ጨበጥ አድርጎ ወደ ደረቱ አስጠግቶ አቀፋት ። ቀረቤታውን በዝምታ ተቀበለችው ። ሲጋራ የያዘችበትን እጅዋን ስቦ ከምታጨሰው ሲጋራ ማገለት ። ጪሱን ወደ ላይ ወደ ጣራው ከገፋው በኋላ ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ

" ለምን ልብሽን ዘጋሽብኝ " አላት

" ለምን እንድንለያይ ትቸኩላለህ " ብላው ትከሻዋን ሰብሰብ አደረገች ።

CamScanner

“ አንድነኙችንን እንጂ መነጣጠላችንን አስቤውም አላውቅምና በጭራሽ አንለያይም ።

“ እኔነቴ የተዋቀረበት ታሪክና ያለኝ ዓላማ ያሸ ሽሃል ”

“ ሰይጣን ብትሆኝም ካንቺ ጋር ሰይጣን ሁኜ ዓላ ማሽን ዓላማዬ አድርጌ የሚመጣውን ችግርም ሆነ ሥቃይ እቀበለዋለሁ ”

“ ጉጉትህ እርግጠኛ ማንነቴንና ገመናዬን መስማቱ ላይ ያደላ ይመስለኛል ብትሰማው ይለውጥሀል እንጂ አይለውጠኝምና እንዲህ ከተጨነቅህበት እነግርሀለሁ ። ሆኖም ሳጣህ ባላዝንም ቅር ሳይለኝ እንደማይቀር እገም ታለሁ ”

“ እንደማንለያይ ይሰማኛል ያንችን ግምት በኔ ውሣኔ ላይ መጫን አትሞክሪ ”

“ ለማንኛውም አረፍ ብለህ አድምጠኝ ” አለችውና ተመልሶ ከነበረበት ቁጭ አለ ። እሷም ፊት ለፊት ከሚታ ያዩበት አቅጣጫ ተቀምጣ ለረዥምም ጊዜ ትክ ብላ አስተ ዋለችው ። ረጋ ብላ ጀመረች ።

“ ሸርሙጣ ነበርኩ ። ሰብአዊ ሞራሌንና አካሌን ክብሬንም ጭምር እጅግ ዝቅ ባደረገው በዚህ ርካሽ ሞያ ላይ የተሰማራሁት ፈቅጄው ወይም ወድጄው አልነበረም። ወደዚህ ርኩሰት የጣለችኝ እናቴ ናት ። ለዚያ ዕድልና ለሚ ያመረቅዝ ጠንቁ ለዳረገችኝ አካል የሰጧት ሲያሜ ያን ሳታል ። በኔ በወንድሜና እህቴ ላይ የወረደችብን የቅ ጣት ጨንገር ብቻ ሳይሆን መሠረት ቦርባሪ ሻህላ ወይም ምስጥ ናት ብል እወዳለሁ ። ዝናና ሙገሳ የሚዘንብላት፤ ለጋስና ሰው ወዳድ የሆነች ፤ በጎረቤቶችዋ ፤ በማኅበርተ

ኞችዋ ዘንድ ተጠሪነት ያላት ሆና ውስጣዊ ኑሮዋ ለኛ ለልጆችዋ ስቃይ የሆነብን ቁጣዋ ዱላዋ ቅጣትዋ ያስመ ረረን አንገታችንን የደፋን ቅስማችን የተሰበረ ነበርን ። አባቴና እሷ ትዳር ብለው ባቀናጁት ሕይወት ውስጥ ልታይ ባይዋና ዋናዋ ሰው እሷ በመሆኗ የአባታችን መኖር አለ መኖር የቀነሰልን ችግር አልነበረም ። ለጋ እድሜያችንን በሰቀቀን በጭንቀት ከወጣነው በኋላ እኔ ስድስተኛ ታላቅ እህቴ ዘጠነኛ ትልቁ ወንድማችን አስረኛ ክፍል ስንደርስ እናትነቷን አክብሮ ለትእዛዝዋ ተንበርክኮ ለፍላጐትዋ ጥሮ በትህትና የቻላት ወንድሜ እሾህ ጠባይዋ እየሷጠጠ ስላደማው ምልጃና ዘመድ በማይፈልግበት መስክ ወታ ደርነት ተቀጥሮ ተለየን ። ቸርነትዋ ጥሩ ሰውነቷ ዘረ ጨዋነትዋ በሚነገርበት ቀዬ ውስጥ እኔና እህቴ በጭ ካኔዋና በችግር ቀጭጨን ስንሰቃይ የሚያውቅልን አል ነበረም ። መልከ መልካም ፥ አንደበተ መልካም ፡ ዘመ ናት አጣቅሳ ወግና ዝና አሞግሳ ግሩም ተራኪ የሆነችው እናታችን ታዛዥዋን አገልጋይዋን እህቴን በፍልጥ ስት ደበድባት ኩላሊትዋ ተጐድቶ በዚያው ሳቢያ ሞተች ። እኔና አባቴም ከቤት ወጥተን ሸሸናት ። ከአባቴ ጋር ቤት ተከራይተን ስንኖር የዘወትር ወሬያችንና ምኞታችን ወን ድሜ ማግኘትና ማየት ነበር ። ከት/ ቤት መልስ ያለኝን ጊዜና ጉልበት የማፈስላቸው ጐረቤታችን መቶ አለቃ ወንድማቸውን እንዲያፋልጉን አድራሻውን እንዲሰጡን ስለ ጠየቁልን መቶ አለቃውም ተስፋ ስለሰጡን ሰው የው ሲመጡ ቡና ለማፍላት ፤ ሲሄዱ ውሻ ከልክዬ ለመሸ ኘት ታዛዥ ሆኘ ማገልገል ቀጠልኩ ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ አመጣጣቸው እየተ ከታተለ ሆነ ። በመጡ ቁጥር ከሌለሁ ተጠርቼ ቡና እንዳፈላ እታዘዛ ለሁ ተሰናብተው ሲወጡ በማይታጐል ሥርዓት እሸኛ

CamScanner

ለሁ ። እጄን አጥብቆ ከመጨበጥ ትከሻዩን ወደማቀፍ፤ከ ጉንጩ ወደ ከንፈሬ ሲሸጋገሩ አነጋገራቸውና ቃላቸው ወን ድሜን ወዲያው እንደሚያዛውሩልኝ ዓይነት ስለነበረ ጉጉቴ ከውጤቱ ላይ ሆኖ የሚያደርጉትን ሁሉ በትዝብት እቀ በል ነበር ። ጊዜው ከመራዘሙ በቀር ያየሁት ያገኘነው ነገር ባለመኖሩ ጥናት አለብኝ እያልኩ መሸሽ ጀመርኩ ። አንድ ቀን ማታ ወንድሜ የሚገኝ በትን አድራሻ እንዳገ ኙልንና ወደዚያም ስንቅና ትጥቅ ይዞ የሚመለስ መኪና ስላለ አባቴን አብረው ለመላክ ማሰባቸውን ሊነግሩን እቤታችን ድረስ አንኳኩተው መጡ ። እኔም አባቴም በነገሩ ተደስተን መሄዱንም ወደን በተባለው መኪና ሳይሆን በባቡር ከሰው ጋር አድርገው ወደ ሀረር ላኩት ። ማታውኑ ከማጠናበት ደርሰው እንደ ለመዱት ከሳሙኝና ወንድሜን እንዲቀየር ለክፍል አዛዡ ደብዳቤ እንደ ጻፉ ካስረዱኝ በኋላ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በመሀረማቸው አፌን አስረው ክብረ ንጽህናዬን አጐደፉት ። በወቅቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ ። በቅርብ ቀን ከወንድሜ ጋር ይመጣል ብዬ የጠበቅሁት አባቴ ከነወሬው ጠፋ ። ጭንቀቴ ስለ በዛ እንደ አውሬ የጠላኋቸውን መቶ አለቃ የአባቴን ጉዳይ ስጠይቃቸው በባዶ ተስፋ ሲያታልሉ ኝና በልጅነት አካሌ ሲዝናኑብኝ ለሶስት ወራት ቆዩ ። አካሌን ለመዝናኛው በረከት ያቀረብኩለት ሌላ ወታ ደር በጨርጨር አውራጃ በዶባ ወረዳ ቢዩ ከረባ ቀበሌ ላይ በሱማሌ ሠርጎ ገቦች አባቴና ወንድሜ ሌሎችም ኢትዮጵያውን መታረዳቸውን አረዳኝ ።

ያችን አባቴ ትቶልኝ የሄደውን ቤት ለሴትኛ አዳ ሪነት ሕይወቴ ማራመጃ መነሻ አደረግኳት ። የሸሸኋ ቸው መቶ አለቃ ጠንቃቸው አብሮኝ ነበረና አካሌ መለ ወጥ ዕድገቴ መፋጠኑን እያሳየ ለሌላ መከራ መዘጋጀቴን

ሲያዩ ባለሁበት አካባቢ መምጣታቸውን አቆሙ ። እር ግዝናዩ እየገፋ ሄዶ ወራዳ ስምና ግምቴን ተላብሼ መንታ ልጆች ተገላገልኩ ። ለመኖር ስል መሸርሞጥ ስለነበረብኝ የአራስ ወግና እንክብካቤ ቀርቶ የምበላው እየጣሁ ወገ ቤን አስሬ ከበር ለመቆም ትግሌን ቀጠልኩ ። ለእቃ መደርደሪያ ብዬ ከተከራየሁት ሣጥን በስተጀርባ በቅር ጫት አልጋ መንትያ ልጆቼን ደረቅ ጡጦ በየአፋቸው ወትፌ ሸሽጌ እደጅ ወይም በሬን ተደግፌ ብርድ እየሸነ ቆጠኝ እቆም ነበር ። እኔም ሆንኩ ቤቴ የእመጫት ጠረን እንዳይኖረንና ሰው እንዳይሸሸኝ ብጥርም ለብዙ ቀናት ቤቴ ጭር ብሎ ያለ አንድ ጉብኝ በቆምኩበት ወገቤ ተን ቀጥቅጦ ከመመለስና አንጀቴን አጥፌ ከመተኛት አልዳ ንኩም ። ያኔ ነው የትላንት ማታው ጭቃ ረጋጩ ጋሽ ሀብቴ ሰዎች እንደ ውሻ ሲያዩኝ ለልጆቼ ወተት መግገ ሳንቲሞች የመጸወቱኝ ። አንዳንዱ እንደ እንስሳ እንኳ ሳይሆን እንደ ዕቃ እያየኝ ፍላጐቱን ካረገበብኝ በኋላ ተጠይፎኝ ተሸሽጐ ሲወጣ ፡ አንዳንዱም መቆሸሼ መደ ሀየቱ ፡ መሸርሞጤ ፡ ወድጄ ያደረግሁት ይመስል ሲደበ ድበኝ ፡ አንዳንዱም የሥቃዩን ዋጋ ከልክሎኝ ይሄዳል ። በዚህ ኑሮዬ ውስጥ ልጆቼ ስድስት ወር ሲሆናቸው ያያ ቸው ሁሉ ሲያዝንላቸው እና ሲያስጠጋቸው ለጉዲፈቻ ብዙዎች ጠይቀውኝ ነበር ። አንጀቴ ቆርጦ ልሰጣቸው አልቻልኩም ። በእመጫትነቴ ገበያ እንዳላጣ ስል ልጆ ቼን ከመደርደሪያው በስተጀርባ እየደበቅሁ ማታ ማታ ያንኑ የረከሰ ሥራዬን ማከናወን ያዝኩ ። አንድ ቀን ሀሊ ናውን ያልሳተ በአለባበሱና በአነጋገሩ ጨዋነቱ የሚ ታይ ሰው ገብቶ ቢራ ጠይቆኝ ለኔም ጋብዞኝ ስንጠጣ እን ዴት ወደዚያ ሥራ ልገባ እንደቻልኩ ለስለስ ባለ ጥያቄ

ሲያናዝዘኝ መቅበጥበጤን ሲያይ እሱም ቢራ ደግሞ
እኔም እንድ ደግም ሲጋብዘኝ በዱቤ ከሱቅ ያመጣሁት
አራት ቢራ አለቀና ሌላ ድጋሚ ሲጠይቀኝ ለማምጣት
ቤቴን ለሱ ትቼ ሮጥኩ ። አራት ጠርሙስ ቢራ ይዤ ስመ
ለስ የጋረድኩትን መደርደሪያ ገፍቶ የቅርጫት አልጋውን
ወደ መሀል ጐትቶ ጣቶቹን እያማታ ልጆቼን ሲያጫውት
አገኘሁት ። በሀፍረትና በድንጋጤ ደርቄ ቀረሁ ። ጡጦው
ከአፋቸው ወድቆ ሲያለቅሱ የድምጻቸውን አቅጣጫ ተከ
ትሎ እንዳያቸውና እንዳወጣቸው ነገረኝ ። ጭራሽ ከተ
ኙበት ተራ በተራ እያነሳ እያጫወተ አቀፋቸው ። ቢቸ
ግረኝ ልብሱ እንዳይቆሸሽና እንዳይሸትበት ነጠላዬን
አጣጥፌ ከጭኑ ላይ ደርቤለት ሁኔታውን ተሸማቅቄ ተመ
ለከትኩት ። ሕጻናቱም የሚያጫውታቸው ስላገኙ እየ
ሳቁ ፈነደቁ ። ስካር የተጫነው መስሎ የታየኝ ሰው ባል
ተወሳገደ አነጋገር በረጋ ህሊና ካለሁበት ሕይወት
በጥረት መላቀቅ እንዳለብኝ እየመከረኝ ከልጆቼ ጋር
ሲጫወት ቆይቶ እንቅልፍ ሲይዛቸው ላባኪንኩብሽ ጊዜ
ነው ብሎ ሃምሳ ብሮች ሰጥቶኝ ሲወጣ ፣ የሕብረተሰቡ
የአስተሳሰብና የኢኮኖሚ አቋም ነጸብራቅ በመሆኔ ልደናገ
ጥና ራሴን ዝቅ አድርጌ ኑሮዬ ከሚያደርስብኝ በደል የበ
ለጠ በደል በራሴ ላይ ማድረስ እንደሌለብኝ ነገር ግን በት
ግል ከዚህ ማጥ መውጣት እንደሚኖርብኝ መክሮኝ ሄደ ።

ከነበርኩበት ርኩስት ለመውጣት ያመላከተኝ ፈር ሩ
ቅና አዳጋች ሆኖ ቢታየኝም ያለምኩትና ያነጣጠርኩት ግን
በዚያች ቀን ምሽት ነበር ። ወዲያው ልጆቼን ኩፍኝ ይዟ
ቸው ታመሙብኝ ። ያኔ ነበር ጋሽ ሀብቴ ጭቃ ረጋጩ ዘግ
ቼው ውዬ ዘግቼው በማመሸው በሬ ስር አሾልከው የአስር
ሣንቲም ዳቦ፣የአስር ሳንቲም ስኳር ፣ የአምስት ሳንቲም ሻይ
ቅጠል የአምስት ሳንቲም ሰንደል ገዝተው የሰጡኝ ። ያኔ

ሰማይ መሬት ተደፍቶብኝ ብቻዬን የመከራ ቀንና ሌሊት
ሳሳልፍ ያጽናኑኝ አይዞሽ ያሉኝ ጋሽ ሀብቴ ጭቃ ረጋጩ
ነበሩ ። ትኩሣቱ ፤ ሣሉ ፤ የዓይን ሕመሙ አጣያፋቸው
ቡናውን ባፈላው ፤ ፈንድሻውን ብበትነው ቆሎውን ብቆ
ላው ኑጉን ብለጠልጠው ሰንደሉን ባጨሰው ያጣደፋቸ
ው ሕመም ቀሜቸው ። ያኔ ነበር ጭቃ ረጋጩ ጋሽ ሀብቴ
ከሣሙና ሣጥን እንጨት የሬሣ ሣጥን ሰርተው የልጆቼን
ሬሣ እስከስላሴ ቤተክርስቲያን ተሸከመው ጉድጓድ ቆፍ
ረው ያቃበሩኝ ። ለሶስት ቀናት ያህል መሰሎቼና ሀብቴ
ዳዲ ካስተዛዘኑኝ በኋላ ወደ ወትሮ ሥራዬ ተመለስኩ ።
ከሁለት ወር በፊት ልጆቼን ያያቸው ሰው ሲመጣ ሆድ
ብሶኝ ፊቴን ዞሬ ብገባም ተከትሎኝ ገብቶ ተቀመጠ ።
ልጆቼን ሊያይ ፈልጎ ቢመላለስ ቤቴ ዝግ እንደነበረ
ከነገረኝ በኋላ ለልጆቼ ያመጣላቸውን ልብስ ሲያቀብለኝ
በሰጠኝ ሹራቦች መካከል ፊቴን ቀብሬ እዬዬን አስነካ
ሁት ። በድንጋጤ የሆንኩት ጠየቀኝና በኩፍኝ በሽታ እንደ
ሞቱብኝ ነገርኩት አብሮኝ አለቀሰ ። ሊረዳኝ ፈቃደኛ
መሆኑን ሲነግረኝ በቤቴ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ዕቃ
ዎች ላዋሱኝና ላበደሩኝ ሰዎች መልሼ ቤቴን የኋሊት
ዘግቼ ያጽናናኝን ሰው ተከትዬ ወደ ሽሮ ሜዳ ቤቱ ሄድኩ።
ከቤቱ እንደደረስን እህቱን ጠርቶ የጓደኛው እህት እንደ
ሆንኩ ነግሯት በትንሿ ክፍል ወ ስጥ ኑሮዬን እንደምመራ
ገልጾ በዘንቢል ኪያዝኩት ልብሴ ሌላ ብርድ ልብስና አን
ሶላ ፍራሽ ከአንደኛው ክፍል ወጥቶልኝ በተባለችው
ክፍል ካለው አልጋ ላይ ተነጥፎልኝ ሰላማዊና ጥገኛ ኑሮ
ዬን መሠረትኩ ።

ከጊዜ በኋላም የሴትኛ አዳሪነትን ሥርወ ታሪክ ለማጥ
ናት ለሚያደርገው ጽሁፉና ጥረቱ የሚደግፍ ታሪክ እንደ
ሆንኩት ነገረኝ ።

እህትና ወንድሞቼን ሰብስቦ የሚያስተዳድረውና የሚያስተምረተው ሰው እኔንም ከቤተሰቡ በመቀላቀል በማንኛውም ረገድ ባልተለየ ሁኔታ እንድማር የሕይወቴ መንገዴን እንዳስተካክል ረዳኝ ። ሰባራ ህሊናዬም እንዲጠገን በምክሩም በተግሣጹም አጠናከረኝ ። የሞት የሽረት ትግሌ ነበርና ፤ እኔም በመራኝ መንገድ በትጋትና በጥረት ተራመድኩ ። ውጤቴም ትጉህና ታዋቂ ተማሪ አደረገኝ ። በኔም ሳቢያ በአሳዳሪነቱ በተያዥነቱ እየተጠራ ሽልማት ወይም ምስጋና ሳገኝ እጅግ ደስ እያለው ዓላማዬን ለሩቅ ለበለጠ ደረጃ እንዳነጣጥር ዘወትር ይመክረኝ ነበር ። የአስተማሪን ታላቅ ሰውነትና የማስተማርን ሙያ ክቡርነት በሚገባ የተገነዘብኩትም በዚያን ወቅት ነው ። እኔም እንደረዳኝ መምህር በሙያ መስኩ ተሰማርቼ ለወገኖቼ ማድረግ የምችለውን ለማበርከት ብዙ ጊዜ ወስኘ ነበር ። የልጆቼን አሟሟት ሳስታውስ ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕጻናት በተላላፊና ጠረርሽኝ በሽታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ እየተቀጠፉ መርገፋቸውን ስለማወቅ ይህንን ሰፊና ጠንቀኛ ችግር ለመቋቋም ስል ወደህክምና ሙያ መሰማራቱን አመንኩበት ። በነበረኝ አጥጋቢ ውጤት የነርስነት ኮርስ መጥቶ ስወዳደር በጥሩ ሁኔታ አልፌ ምኞቴን እውን ለማድረግ ተመቻቸልኝ ። ወደ ጐንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ ሄጄ የአስታማሚነት ትምህርትና ኮርስ አጠናቅቄ በሙያው ላይ ዓመታት አሳለፍኩ ።

ኑሮዬን ዋስትና ባለው መልኩ ማራመድ ወይም ማደራጀት ብችልም የህሊናዬ ቁስል አሁንም ስለሚደማ አክሜ ለማዳን የሙያዬ ብቃት አልረዳኝም ። ደም በደም ይነጻል የሚል እምነት ስላለኝ በዚያ ደም ተለቃልቄ ፈውስ ለማግኘት የማይበርድ ምኞትና እቅድ አለኝ ። ጊዜና ሁኔታ አመቻችተው ለበደል ቢዳርጉኝም ፤ በችግር ጫና

ብልጫ ብልጦች ሕይወቴን ቢያወላግዱትም ፤ አካሌ እንጂ መንፈሴ በበታችነት አልወደቀምና በሴትነት ተፈጥሮዬ የአበሻነት ኩራቴ ልቤን ሞልቶታል ።

ውርደት እንደሚጠየፉት ጀግኖች በደል እየከረፋኝ እኔነቴ ለበቀል እንዳሸመቀ ልቤ የቋተው ቋሳም እንደደደረ ነው ።

እስከዚያው ድረስ የመንፈስ እረፍት አይኖረኝም ። ሠምሮልኝ እስካደርገው ከሰዎች ጋር ያለኝ ግንኙነትና ቀረቤታ ውሱን ሊሆን የግድ ነው ። ስሜቴን የሚካፈለኝ ወይም የምከፍልበት ሲጋራዬ ሲሆን የምመካበትም ደምመላሽ አለኝ ። የባሩድ ጪስ ባያውደውም እንዳልዛገ ተስፋ አደርጋለሁ ። እንግዲህ እኔና ገመናዬ ይህንን እንመስላለን ። ከማንም ፍላጐትና ዓላማ ጋር የማይጣጣም መሆኑ ነው ። ስለዚህ መንገዳችን መድረሻችን ለየቅል በመሆኑ ትዝታ ተካፍለን በየመስመራችን ልንጓዝ ግድነውና ልታውቀኝ እንደቻኮ ልክ ልንለያይም በቅተናል ። ” ብላው ተነሳች ።

ከወፍራሙ የወላሞ ሸማ መጋረጃ በስተጀርባ ለጥቂት ጊዜ ከቆየች በኋላ ከጊዜ ብዛት የወየበ ፎቶግራፍ አምጥታ አሳየችው ። ከፍርግርግ የእንጨት አጥር ላይ ቡራቡሬ ብርድልብስ ተወጥሮ ከበስተጀርባቸው ይታያል ። መንትያ ልጆችዋ ጐን ለጐን ተቀምጠው ይታዩበታል ። ተመሳሳይና የሚያሳዝኑ መንትዮች ነበሩ ። በአክብሮት የተቀበለውን ፎቶግራፍ በአዘኔታ ለብዙ ደቂቆች ልብ ብሎ ተመለከተው ። በሰማው ሁኔታ ሁሉ እያዘነ ፤ በተረከችለት እንግልትና ሥቃይ ውስጥ ራሱን እየተካ የመከራዋን ክብደቱንና ጥልቀቱን ለመመዘን እየሞከረ ፤ የገፋችውን የችግር ዕድሜ ክፋት ተረዳላት ። ልቡ ግን በእርግጥም ርኩሰት በነበረው የማለዳ ሕይወቷ አልተጠየፋትም ። ይልቁ

ንም በጥንካሬዋና በዓላማዋ ጽናት ኢድንቋታል ። እሱንም አንዳች ነገር ተጭኖ እንዳደከመው ሁሉ አካሉም ህሊና ውም ዝሎ ከተቀመጠበት በእርጋታ ተነስቶ የያዘውን ፎቶግራፍ ሊመልስላት መጋረጃውን ገልጦ ወደ መኝታ ክፍሏ ገባ ። ትራስዋ ላይ ፊትዋን ደፍታ አጐንብሳ አገኛት ። በሆስፒታሉ ቢሮዋ ውስጥ ሥነ ሥርዓት ሳለመጣስ ብሎ ተቆጥቦ እንዳነጋገራት ሁሉ የቃላት ጥያቄ ወይም ማጽናኛ አልለገሳትም ። በጠንካራ ክንዶቹ አቅፎ ቂምና ሀዘን የቦረቦሩትን አካልዋን በእጆቹ ኋላም በከናፍሩ ዳሰሳቸው ። ለዓላማዋ መሳካት ስትል የራስዋ የሆነ የአኗኗር ዘይቤና ጠባይ ብትፈጥርም ፤ ሰብአዊ ስሜቷን ለመግታት ብትጥርም ፤ የተፈጥሮ ኃይል ሚዛን በማድላቱ ቁጡ ሰውነቷም ሆነ አንደበቷ በመኩሪያ እቅፍ ውስጥ ገረመ ። ሰፊው ደረቱ ሥር አቅፎ በርኅራኄው ተጨንቆ ስሜቷን ለመካፈል ጣረ ። የደም ዑደት በሚረጨው ግለትና ንዝረት ፤ የአካል ንክኪ በፈጠረው ስሜታዊ ንግግር ተደማመጡበት ። የህሊና እውነታቸውን በዝምታ ተውጠው መፈላለግ ባጠነከረው አካላዊ አንድነታቸው ተወያዩበት ። ሺህ ቃላት የማይገልጹትን ሀሳቡን በእጆቹ አስረዳት ። ደረቱ ላይ የተደፋውን ጭንቅላትዋን ቀና አድርጐ ትናንሽ ዐይኖችዋን በተራ በተራ ሳማቸው ። ወዲያውም ከደስታ በመነጨ ፈገግታው ፊቱን አብርቶ አዘቅዝቆ እየ ተመለከታት ፤ “ ደመኛሽን እኔም እፋረደዋለሁ ። መንገድሽ መንገዴ ነው ፤ የሕይወቴም ፋና ነሽ ። ” አላት ።

እቅፉ ውስጥ እንዳለች ከት ብላ ሳቀች ። የወትሮው እሷነቷ ተመልሶ በገጽታዋም ሆነ በሳቅዋ ውስጥ ተከሰተ ። “ አቶ መኩሪያ ” አለችው የተናገረው ሀሳብ በገለጸችለት ታሪኳ የታገደ መሆኑን ለማስገንዘብ ፤

“ አቶ መኩሪያ ሊያስከፋ ወይም ሊያሳዝን የሚችል ታሪኬን ስተርክልህ በልበ ፍንቅልነት ተነሳስተህ እንድታጽናናኝ ወይም ከነተበከለ ሕይወቴ እንድትቀበለኝ ለማስተዛዘንም አይደለም ። ለሚስትነት አልተፈጠርኩም ። እናትነትም አልተሰጠኝም ። የእድል በረከትዋ ጠብታዋ አልወደቀብኝም ። ስለዚህም በተፈጥሮው ቁልቁል የሚወርደው ጅረት እንኳ ኔ ዘንድ ሲደርስ ሽቅብ የሚመለስብኝ ነኝና ማንም ከችግሬ እንዲዘፈቅ አልለምንም አልጋብዝም። መንገዳችን ለየቅል ነው ። ሆኖም በየአቅጣጫችን እየ ተጓዝን በመልካም የማንተሳሰብበት ምክንያት አይኖርም ። እና አይሆንም ። ” ብላ እንደገና ፈርጠም ባለ ሁኔታ ከእቅፉ ወጥታ ወደ እንግዳ መቀበያዋ ክፍል ትታው አለፈች ። ተከትሏት ወጣ ።

“ ፋኑ ሠናይ እድላችንን ልንፈጥራት እንችላለን ”
“ አንችልም ”

“ እንችላለን ። የነፍስሽን መቅበዝበዝ የህሊናሽን ድማት ከኔ የበለጠ የተረዳ እንደሌለ ሁሉ የልቤን ፍላጎት የእኔነቴን ግምት ካንቺ የበለጠ የሚያውቅልኝ አላገኝሁም ። የተፈጠርሽው ለኔ ነው ። ከኔ የሚነጥልሽ ኃይል አይኖርም ”

“ የወደደ ሁሉ የሚያቀርበው በረከት ነው ። ባዶ ቃላት እንዳልሆነ ግን አውቃለሁ ። ሆኖም እኔን ከመንገዴ ማርከው አይመልሱኝም ። ”
“ ተቀበይኝ ”
“ ምኑን ”
“ አካልና መንፈሴን ሙሉ ፈቃዴንም ጭምር ”
“ አይሆንም ”

" ይሆናል ፣ እምነትሽን ልጨብጠው እምነቴንም ጨብጪው " አላትና አሁንም ከቃላት ይልቅ በሁኔታ የልቡን ስሜት ሊገልጥላት ሽቶ በቆመችበት አቀፋት ። በሞቀ እስትንፋሱ በጋለ እጁ አካልዋን ዳበሰው በገጽ ታዋ ላይ በዐይኖቹ ተመላለሰባት ። የሱ ስሜት በውሳኔው ተቀጣጥሎ የነዲዱ ስሜት ፊቱን በፈገግታ አብርቶት እን ደልማዳቸው ግራና ቀኝ ጉንጮቹ ተሰርጉደው ይታያሉ ። ያለችውን ብትልም አንዳች ለውጥ ሳያሳይ ቀረቤታውን በማጠናከሩ ልብዋ በአዘኔታም ይሁን በመውደድ ገና ከመጀመሪያውም ቢሆን እየተከፈለ ስለነበር የህሊና ሙ ግት ይዛ ዝም አለች ።

" የሕይወቴ ፋና ነሽ " መሀል አናቷን ሳመው

" አስብ "

" አስቢያለሁ "

" ደመላሼ ልትሆን ፣ ግብረ አበሬ ልትሆን ፣ ለአመጼ ክንድህን ልታነሳ በእውነት ትወዳለህ ? "

" በሙሉ ልቤ እቀበለዋለሁ " በደለኝ ባለችው መቶ አለቃ ላይ በምን ሁኔታ እንደሚዘምት ገና አላሰላሰለውም ።

" እኔ ግን እድሌን አላምናትም ። ከሆነልን እሺ " ቀና ብላ የጉንጮቹን ስርጉዳት በየተራ ሳመቻቸው ።

ፍቅር በሀሴት አክናፍዋ ወርዳ በሁለቱ አካልና መን ፈስ ላይ አረበበች ። አንዱ የሌላውን ባዶነት በመሙላት የአንድ አካል አቋም ለመፍጠር ተዋሃዱ ። የልብ ንግግር የመንፈስ ጨዋታ ይዘው በተፈጠረው አንድነት ህሊና ቸው ባለፈውና በወደፊቱ ሁኔታቸው ውስጥ በብርቱ ተመላለሰ ። በውጫዊ እይታ ተቃቅፈው ተደጋግፈው በእርጋታና በዝምታ የሰከኑ ቢመስሉም ውስጣዊ የስሜት

ግለትና የመንፈስ ስደት አድክሟቸው ቆዩ ። ቤቱም ጸጥታ ሰፍኖበት ቆየ ። ምንቴ ስትደርስ ነፍሷ የቸኮለችበ ትን ውጤት ጠይቃ ሳይሆን አይታ ተረዳች ። ልባዊ ደስ ታዋን በሣቅ ብቻ ሳይሆን በልቅሶ ገለጠችው ።

ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ምንቴ የእናትነት ስሜት ሰር ጿት ለእቅዱ ስምረት የሚገባውን ሁሉ ልታደርግ ኃላፊ ነቱ ከደስታ ጋራ ተጫናት ። መኩሪያና ሲስተር ተቀም ጠው የልባቸው ስሜት ነጸብራቅ በአካላቸው ላይ ጸዳሉን አላብሶ እየታየ የደስ ደሱን ቤት ያፈራውንና በቤት የተገ ኘውን ሁሉ እያቀረበች ትንሽና ሞቅ ያለች ግብዣ ምን ተስኖት አዘጋጀች ። ጊዜው እጅግ መሽቶ ለዐይን ቢይዝም ለመሄድ አለተቻኮለም።መኩሪያ በእፎይታና በደስታ ግዙፍ አካሉን አዝናንቶ ተቀምጧል ። በመካከሉ ስልክ ተደወለና ባለአደራዋ አስታማሚ ሲስተርን መምጣትዋን ፈለገች ። የበሽተኛው አስታማሚ ሆነው የሚገኙት አቶ ሀብቴ እንድ ትመጣላቸው የጠየቁ መሆኑን በመስማትዋ ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ተነሳች ። በመኩሪያ መኪና በካዛንችስ በኩል ታጥፈው ኢዮቤልዩ ቤተመንግሥትን በስተግራ ትተው ቁልቁል ወርደው ወደቀኝ እንደታጠፉ በርቀት አየቻቸው። አቶ ሀብቴ ዳዲ ከሆስፒታሉ ደጃፍ ተቀምጠው ነበር ። ድንጋጤ የታከለበትን ሰላምታዋን እምብዛም ያዳመጡት አይመስልም ነበር ። መኩሪያንና ሲስተርን ቀና ብለው አላዩዋቸውም አካላቸው መንፈሳቸው በሀዘን ተሰብሯል ። በመኪና አደጋ የተጎዳው ጓደኛቸውን በማዘጋጃ ቤት እርዳታ ከሰዓት በፊት በጴጥሮስ ቤተክርስቲያን ቀብረው መመለሳቸውን ከነገሯቸው በኋላ ሀብቴ ዳዲ ጭንቅና ትክዝ ብለው ሲስተርን ይቅርታ ጠየቋት ። ስለምን እንደ ሚናገሩ ለሲስተርም ሆነ ለመኩሪያ ሊገባቸው አልቻለም ።